# በሀገር ሉዓላዊነት ላይ ልዩነት የለም

ርዕሰ አንቀጽ
አዲስ ዘመን
ህዳር 18/1999 ዓ.ም

ኢትዮጵያውያን የጦርነትን አስከፊነት ከማንም በላይ ደጋግመን አይተነዋል። ይህም በጦርነት የሚገኝ ጥቅም፣በጦርነት የሚሰበሰብ ትርፍ አለመኖሩን ለማወቅ ዕድል ሰጥቶናል። በዚህም የተነሳ ከጦርነት እርቀን፣ ግጭትን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት አልመን፣ ከጎረቤቶቻችን ጋር በጋራ ጥቅም ላይ የተገነባ ወዳጅነትን መስርተን ለመኖር ጥረት አድርገናል። ለዚህም የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን ጉልህ ማስረጃችን ነው።

ነገር ግን በሰላም ተከባብሮ የመኖር መርህን መከተላችን፣ ግጭትን እና አለመግባባትን በውይይት ለመፍታት መጣራችን የምንፈልገውን ሰላም አላስገኘልንም። ምክንያቱም በዋናነት ጠላታችን ድህነት መሆኑን አምነን ጦርነታችን ከኋላቀርነት ጋር መሆኑን ተገንዝበን ለልማት ደፋ ቀና ስንል የኤርትራ መንግሥት ጦር አዝምቶብናል።

ይህ በእርግጥም የአንድ ወገን ሰላም ፈላጊነት ብቻውን የሚያመጣው ለውጥ አለመኖሩን አመላካች ነበር። ይህም ሆኖ ግን በኢትዮጵያ በኩል የኤርትራን መንግሥት ጠብ አጫሪነት በመታገስ ችግሩን በውይይት ለመፍታት ያላሰለሰ ጥረት ተደርጓል። የሁለቱ ሀገሮች ግጭት ድህነትን ከማባባስ ያለፈ ጥቅም እንደሌለው በመገንዘብ የመካሪ ያለህ ብለናል።በኤርትራ መንግሥት በኩል ግን ይህ ሰላም ፈላጊነት ብዙም ትርጉም አልነበረውም። ስለዚህም የኢትዮጵያ ህዝብ እና መንግሥት የሀገራቸውን ሉዓላዊነት ለማስከበር ወደ ጦርነት ለመግባት ተገደዋል። በዚህም በድርድር፣ በውይይት፣ b>MGLÂ ተሞክሮ አልደፈርም ያለው ወራሪ ኃይል የራሱን ሀገር እንኳን ለማስከበር ብቃት እንደሌለው እንዲገነዘብ ተደርጓል።

በዚህ ወቅት ህዝባችን የሀገሩ ሉዓላዊነት መደፈር አስቆጥቶት ከዳር ዳር ተንቀሳቅሷል። ከመከላከያ ሠራዊት ጎን በመሰለፍ ለሀገሩ ለዓላዊነት መስዋዕትነት ለመክፈል ያለውን ቀናኢነት አሳይቷል። በደጀንነትም ድርሻውን ተወጥቷል።

ወራሪW የኤርትራ ኃይል ይህንን ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸው ሉዓላዊነት መከበር ያላቸውን ቁርጠኝነት በግልፅ አይቷል። መቼም ቢሆን ከዚህ ህዝብ ጋር ተዋግቶ እንደማያተርፍም ትምህርት አግኝቷል። ይሁን እንጂ ዛሬም ቢሆን ከጠብ አጫሪነቱ አልታቀበም። በቀጥታ ወረራ ለመፈጸም ባይደፍርም ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎችን በማሰልጠን፣ በማስተባበር እና አለንላችሁ በማለት ሰላማችንን ከማወክ አልተቆጠበም።

ለዚህ የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት ጅሃዲስት መሪዎች የሰሞኑ ድርጊት ጉልህ ማስረጃ ነው። ከአሥራ ስድስት ዓመት በላይ መንግሥት አልባ የሆነችውን ሀገር ማረጋጋት ሲገባቸው በሻዕቢያ ፊት አውራሪነት በኢትዮጵያ ላይ ጅሀድ አውጀዋል።

እነዚህ አክራሪ ኃይሎች ኢትዮጵያ የሶማሊያ ህዝብ የክፉ ቀን ወዳጅ መሆኗን ዘንግተው፤ bመንግሥት አልባዋ ሶማሊያ ሰላም እንዲሰፍን ያደረገችውን ጥረት ዋጋ አሳጥተው የሻዕቢያ ተላላኪ ሆነዋል።

ይህም ሆኖ ግን ኢትዮጵያ ከተለመደው የሰላም ፈላጊነት አቋሟ ለውጥ አላሳየችም። ሶማሊያውያን ለዓመታት የዘለቀውን የእርስ በርስ ጦርነት አቁመው በሀገራቸው ሰላም እንዲያሰፍኑ፣ ለዚህም በዓለም ሀገሮች ተቀባይነት ካገኘው የሽግግር መንግሥት ጋር አብረው እንዲሰሩ ከመምከር አልታቀበችም።

አክራሪው ኃይል ጦርነት ሲያውጅብንም፣ሉዓላዊነታችንን ለመድፈር ሲንቀሳቀስም ችግሩን በውይይት እንፍታው ከማለት አልተቆጠበችም። ነገር ግን ይህ ሰላም ፈላጊነት እንደተለመደው ውጤት አላስገኘም። የሞቃዲሾን አክራሪ አመራሮች የእብሪት እርምጃ ማስታገስ አልቻለም።

ስለዚህም ወቅቱ የሀገር ሉዓላዊነት ስጋት ውስጥ የወደቀበት፣ የሀገራችን ሰላም ሽብርተኝነትን በሚያራምዱ ኃይሎች ሊታወክ የተቃረበበት በመሆኑ ሰሞኑን፣ መንግሥት በጉዳዩ ላይ ያለውን አቋም ግልፅ አድርጓል። የሸሪአ ፍርድ ቤቶች ኅብረት አክራሪ መሪዎች በሀገራችን ላይ ያወጁት ጦርነት መቀልበስ እንዳለበት እንደሚያምንም ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሰጡት ማብራሪያ አስገንዝበዋል።

በዚህ ሂደትም የምክር ቤቱ አባላት ጉዳዩን ከተለያየ አቅጣጫ በመመልከት ጠቃሚ ነው ያሉትን ውሳኔ አስተላልፈዋል። ምክር ቤቱ በብዙኃን ፓርቲ ሥርዓት የተመሰረተ፣ የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶችን የሚያራምዱ ፓርቲዎችን ያቀፈ ቢሆንም ሁሉም ፓርቲዎች በሀገር ሉዓላዊነት መከበር ላይ ምንም ዓይነት ልዩነት እንደሌላቸው በግልጽ አሳይተዋል።

የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ቢኖራቸውም ገዥውም ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሉዓላዊነት ጉዳይ ከፖለቲካ ፓርቲዎች  ሽኩቻ በላይ ነው የሚል አቋምም አራምደዋል። በዚህም ኢትዮጵያውያን በሀገራችን ሉዓላዊነት ላይ አንድ መሆናችንን የሚያንፀባርቅ ለጠላቶቻችን ጠንካራና ግልጽ መልዕክት አስተላልፈናል።

በእርግጥም ኢትዮጵያውያን ልዩነታችን መብታችን ነው። የብዙኀ ፓርቲ ሥርዓት መኅልበትም ይህን በልዩነታችን ላይ የተመሰረተውን አንድነታችንን አጠናክሮታል። በሀገር ሉዓላዊነት ላይ ልዩነት የለም የሚለው አቋማችንም ይህን ያንፀባርቃል።